
ፍጽምና የመጠበቅ ዝንባሌን ማሸነፍ የሚቻለው እንዴት ነው?

ፍጽምና የሚጠብቁ ሰዎች ማንኛውንም ስህተት ቸል ብሎ ማለፍ ይከብዳቸዋል፤ ይህም በራሳቸውም ሆነ በሌሎች ሰዎች እንዲበሳጩ ያደርጋቸዋል። አንተስ ከራስህም ሆነ ከሌሎች ፍጽምናን ትጠብቃለህ? ከሆነ የሚከተሉትን ሐሳቦች ተግባራዊ ለማድረግ ሞክር።

1 ችግሩን ለይተህ ለማወቅ ሞክር

ፍጽምና የመጠበቅ ዝንባሌ እንዲታይብህ የሚያደርጉት ሁኔታዎች የትኞቹ ናቸው?



ትምህርት ቤት

(ፈተና ካልደፈንክ በጣም ይከፋሃል።)



ቤት ውስጥ

(ክፍልህን ስታስተካክል ሁሉም ነገር በሥርዓት እንዲቀመጥ ትፈልጋለህ። ትንሽ ዝንፍ ያለ ነገር እንኳ ካየህ ያበሳጭሃል።)



ከጓደኞችህ ጋር ስትሆን

(ሌሎች ሰዎች በተለይ ደግሞ በጣም የምትቀርባቸው ሰዎች የሚሠሩትን ስህተት ፈጽሞ መታገሥ አትችልም።)



ሌሎች ሁኔታዎች

_____

_____

ፍጽምና የመጠበቅ ዝንባሌ እንዲታይብህ ስለሚያደርጉት ሁኔታዎች ለማሰብ ሞክር። ከእነዚህ ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ ፍጽምና የመጠበቅ ዝንባሌ የምታሳየው እንዴት ነው?

_____

_____

_____

www.jw.org © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

2 ይህን ዝንባሌ ለማሸነፍ ጥረት አድርግ

መጽሐፍ ቅዱስ ‘ከሰማይ የሆነው ጥበብ ምክንያታዊ ነው’ ይላል። (ያዕቆብ 3:17) ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ ከራስህም ሆነ ከሌሎች ሰዎች በምትጠብቀው ነገር ረገድ ምክንያታዊ መሆን የምትችለው እንዴት ነው?

▸ _____

_____

ከማድረግ ይልቅ

▸ _____

_____

ማድረግ እችላለሁ

_____



3 ጥቅስ ምረጥ

ከአንተ ሁኔታ ጋር ይበልጥ የሚስማማው የትኛው ጥቅስ ነው?

- ○ “ልክህን አውቀህ ከአምላክህ ጋር [ሂድ]።”—ሚክያስ 6:8
- ○ “ያህ ሆይ፣ አንተ ስህተትን የምትከታተል ቢሆን ኖሮ፣ ይሖዋ ሆይ፣ ማን ሊቆም ይችል ነበር?”—መዝሙር 130:3
- ○ “ሁልጊዜ ጥሩ ነገር የሚያደርግ . . . ጻድቅ ሰው በምድር ላይ የለም።”—መክብብ 7:20
- ○ “ሁሉም ኃጢአት ሠርተዋል፤ የአምላክንም ክብር ማንጸባረቅ ተስኗቸዋል።”—ሮም 3:23
- ○ “ምክንያታዊነታችሁ በሰው ሁሉ ዘንድ የታወቀ ይሁን።” —ፊልጵስዩስ 4:5

የመረጥከው ጥቅስ ፍጽምና የመጠበቅ ዝንባሌን አንድታሸንፍ ሊረዳህ የሚችለው አንዴት ነው?

_____

_____

_____

_____

_____

_____

_____

_____

www.jw.org © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

4 አርዓያ ሊሆንህ የሚችል ሰው ምረጥ

ምክንያታዊ በመሆን ረገድ አርዓያ አድርገህ የምትመርጠው ማንን ነው? ለምንስ?





“ፍጽምና የምጠብቅ ዓይነት ሰው እንደሆንኩ ሲሰማኝ የማደንቃቸውን ሰዎች ለማሰብ እሞክራለሁ። እነዚህን ሰዎች የማደንቅበት አንዱ ምክንያት አብሬያቸው ስሆን ነፃነት የሚሰማኝ መሆኑ ነው። ሌሎችም ስለ እኔ እንዲህ እንዲሰማቸው አፈልጋለሁ፤ ይህም ፍጽምና የመጠበቅ ዝንባሌን ለማስወገድ ጥረት እንዳደርግ ያነሳሳኛል።”—አና



5 ግብ አውጣ

ፍጽምና የመጠበቅ ዝንባሌን ለማሸነፍ ምን ግብ ልታወጣ ትችላለህ?

“አንድ ነገር እንዳሰብከው ሳይሆን ሲቀር የምትችለውን ሁሉ እንዳደረግክ ለማሰብ ሞክር። አዎንታዊ በሆነው ነገር ላይ አተኩር። ያሰብከው ነገር ሳይሰካ ሲቀር ካጋጠመህ ሁኔታ ትምህርት አግኝተህ ለማለፍ ጥረት አድርግ።”—ካራ

www.jw.org © 2017 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania